# ምን ታዝባችኋል ! ከቆዬ ስንክሳር
## (ታዛቢዎች)
## ሙግት

መሰንበት ደግ ነው ሁሉን ያሳያል ይባላል። እውነትም መሰንበት ደግ በመሆኑ የሚለመነው ጤናና እድሜ ነውና እኛም እድለኞች ሆነን በቆየንበት እድሜ የታዘብነው ነገር ቢኖረን ልናካፍላችሁ ወደድን። ምናልባት እናንተም ታዝባችሁ ከሆነ እሰየው እያልን ጨዋታችን ጣማችሁ አልጣማችሁ ወደ ጨዋታችን ልንደባልቃችሁ ፈቀድን። ጨዋታ በሰማይ ደጅ አይገኝም ተብሏልና።

በርዕሱ ላይ እንዳስቀመጥነው ጨዋታችን ሙግት ነው። ሙግቱ ደግሞ እውነተኛ ሙግት ነው። በተለያየ ጊዜ የተካሄደ፣ የተለያዩ ተሟጋቾች የታዩበት፣ ከሳሽና ተከሳሽ ረችና ተረች በመሆን ፋይላቸውን እየዘጉ፣ የቀጠሉበት ሂደት ነው። እረጅም ዓመት ወስዷል። ዳኞች፣ ተሟጋቾችና ጠበቃዎችም እንዲሁ። ሁሉም ተሟጋቾች በየጊዜው በተለያየ ወቅት ይቅረቡ እንጅ እኛ እንደታዘብነው ተከሳሾቹ የተለያዩ ሲሆኑ ከሳሾቹ ግን ሁልጊዜ አንድ ሆነው ግን ስማቸውና የክሳቸው ይዘትም (እንደ ገጠማቸው ተሟጋች ዓይነት) ይቀያየራል። ዋናው ግን ከሳሾቹ አንድም ይሁኑ ተበድለናል እስካሉ ድረስ ክስ የመመስረት መብት እንዳላቸው እኛ ታዛቢዎች እናምናለን በዳኞችና በችሎቱ አደባባይ እምነት ስላለን። ይህ በዚህ እንዳለ ከሳሾቹ ሁሌ እየከሰሱ ክሳቸው በዳኞች ፊት እየታየና እየተመረመረ፣ ዳኞች በሚሰጡት ፍርድ ውድቅ እየሆነ፣ እየተረቱ ሲወጡም ተመልክተናል። ግን የዳኞቹን ውሳኔ ከሳሾቹ ሁሌም አያከብሩም። ከዚያም በኋላ ቢሆን በተለያዩ ጉዳዮች ነገር ግን ተመሳሳይነት ባላቸው ነገሮች ላይ ክስ በመክፈት ያለ መታከት በሙግቱ አደባባይ ላይ አውራ ሆነው መቅረባቸው አልቀረም። ብርታታቸው የሚያስገርም ነው። ዛሬ እኛ ልንተርክ የተነሳነው ቁም ነገር ከሳሽና ተከሳሽ ተሟግተው፣ በትክክለኛ ዳኛ፣ አብዛኛው ህዝብ (ሁሉም ማለት ይቻላል) በተከታተለው ችሎት እየተገኘተን የተመለከትነው ሙግት፣ ምን ያህል አስተማሪ እንደሆነ እናንተም ታዩት ዘንድ በማሰብ ፣ እናንተም እንደኛ በሙግቱ አደባባይ እየተገኛችሁ የምትታዘቡትን እንድንጨዋወት ፈልገን ነው።

ከሳሾቹ ሁሌ በጠበቃ ሲከራከሩ፣ ተከሳሾቹ ግን አብዛኛዎቹ ያለጠበቃ ነው ለመከራከር የሚሞክሩት። ቢሆንም ከሳሽና ተከሳሽ በውሳኔያቸው መሰረት የሙግት ፋይላቸውን እየከፈቱ ተከራክረዋል። እኛ የዳኞችን ትዕግስትና ችሎታ፣ ፍትህም እንዴት እንደተስተናገደች ተመልክተን ዳኞችን አድንቀናል። የፍትህ አደባባዩ ራሱ ጥንት ጀምሮ ተሟጋቾችን በትክክለኛው (ከፍትህ አንፃር) ሲያስተናግድ የኖረ በመሆኑ፣ የጥንት፣ አዛውንትና አዕሩግም ነው።

የሙግቱ ጊዜ የቆየና ታሪኩም የቆየ ቢሆንም አሁንም ከሳሾቹ አንረታም በማለት በተለያዩ ድርጅቶች ላይ በተመሳሳይ መንገድ እስካሁን የክስ ፋይል በመክፈት የህልውናቸው ማቆያ መሳሪያ አድርገውታል። እንደታዛቢዎች እምነት እነርሱን ተቃዋሚ የሆኑና ለእነርሱ

የሚያስጓቸውን የሚያጠቁበት፣ በአንፃሩም የነርሱ ተቃዋሚ የሆኑ ኃይሎች በሙሉ በአንድ ላይ እንዳይመጡና ከስሾሹቹ ላይ እንዳያትኩሩ የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው ብለን እናምናለን። ይህ የእኛ እይታ ነው።

ሙግቱ ምንድን ነው? ተሟጋቾቹስ እነማን ናቸው? ዳኛውስ ማን ነው? የችሎቱ አደባባይስ የት ነው? የሚሉትና የመሳሰሉትን ትከታተሉት ዘንድ ወደ ችሎቱ አደባባይ እንውሰዳችሁ። በተከታታይ እድሜ ከሰጠንም የያንዳንዱን ተካሳሽና ከሳሽ የሙግት ውሎ ለትምህርታዊነቱ እናቀርብላችኋለን። ለዛሬው የኢህአፓና የኢህዴን፣ የመአህድና የብአዴንን የክርክር ሂደት እንደቀደም ተከተላቸው ይዘን ቀርበናል። የመጀመሪያው እነሆ! መልካም ንባብ።

| | |
|---|---|
| የከሳሽ ስም | ኢህዴን(የኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) |
| የተከሳሽ ስም | ኢህአፓ(የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ) |
| ዳኛ | የኢትዮጵያ ህዝብ |
| ችሎት አደባባይ | አንጋፋዋ ኢትዮጵያ |
| ፋይሉ የተከፈተበት ጊዜ | ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር |
| ፋይሉ የተዘጋበት ጊዜ | 1984/85ዓ.ም ኢትዮጵያ አቆጣጠር |

ከላይ እንደተመለከተው፥ ከሳሽ የሆነው ኢህዴን፣ ለክስ ያበቃኛል ብሎ ክስ የከፈተበት ድርጅት፣ በ1967ዓ.ም እንደ ኢት አቆጣጠር የተመሰረተው ''ኢህአፓ'' ላይ ሲሆን፣ የክሱ ይዘት ''ኢህአፓ የሚባለው ድርጅት'' በአሁኑ ሰዓት የለም። ይህ ድርጅት በራሱ ችግር ምክንያት በፈጠረው ቀውስ ይታገልበት የነበረውን ዓላማ መቀጠል ስለአልቻለ፣ እንደ ቀድሞው ኢህአፓ ሆኖ መቀጠል አይችልም። ከዚህ በኋላም ''እውነተኛውን ኢህአፓ'' ወክሎ መታገል አይቻለውም። ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ''እውነተኛውን ኢህአፓ'' የምንወክለው እኛ ነንና ከዛሬ ጀምሮ ህጋዊውና ''እውነተኛው ኢህአፓዎች '' እኛ ነን በማለት የመከራከሪያ ፋይሉን የከፈተው በጠበቃው ኢህአዴግ አማካኝነት ነው። ኢህዴን በማከልም ''ኢህአፓ'' የሚለው ስምም ለኔ ይገባል በማለት ዳኞችን ተማፅኗል።

ተከሳሽ የሆነው ድርጅት ኢህአፓ ደግሞ ያለጠበቃ ሲከራከር የመከራከሪያው አብይ ጉዳይ፣ <u>ክቡር ዳኞች ሆይ!</u> ''ጀማሪው ኢህአፓ እኔ ነኝ አሁንም አለሁ።'' እኔን ''ትክክለኛ ያልሆነና ከሚታገልበት ዓላማ አፈንግጧል'' በማለት ሊከሰኝ የተነሳው ኢህዴን ፣ ቀድሞ ነገር እኔን ከሳሽ ሆኖ ለመቅረብ እንደ ድርጅት ድርጅታዊ ነፃነት የለውም። ሁለተኛው አብይ ጉዳይ ደግሞ ኢህዴን ኢህአፓን ለመክሰስ የሞራል ብቃት የለውም። አለመኖሩን ደግሞ አሁን ኢህዴን እየሰራ ያለው ተግባሩ እያሳየን፣ ወደፊትም እድሜ ከሰጠን የምናየውና ክቡር ዳኞችም የሚታዩት ሰለሆነ ፍርዱን ለክቡር ዳኞች እተወዋለሁ። የሆነ ሆኖ ግን ኢህአፓ መጀመሪያም ሲነሳ የተነሳበት ዓላማ፣ የህዝብ መንግስት እንዲቋቋም፣ የህግ የበላይነት እንዲኖር፣ የዜጎች መበት እንዲከበር፣ የጤናና የትምህርት እድል ለሁሉም እንዲዳረስ፣ ኢትዮጵያ የሁሉም ናትና ዜጎቿ ሁሉ በሁሉም መስክ፣ በእድገቷ በልማቷ፣

በሰላሟ፣ በጥንካሬዋ፣ በደስታዋም ሆነ በችግሯ ሁሉ እኩል የሚጨንቁላትና፣ እኩል የሚስተናገዱባት፣ ዜጎቿ ሁሉ እኩል የሚሳተፉባት ያገባናልም የሚሉባት አገር ልትሆን ይገባል የሚል ስለሆነ፣ ይህ በኢትዮጵያ ወስጥ እውን የሚሆንበት ዓላማውን ይዞ በሚችለው መንገድና በሚያመቸው ትግል እየቀጠለ ያለ መሆኑን፣ በቁርጠኝነት ለከሳሹ ኢህዴን ስነግረው፣ በተከበሩት ዳኞች ፊት በመሆኑ በልበ ሙሉነት ነው። ስለዚህ ኢህአፓ አሁንም በትግል ላይ ስላለ ሌላ "ወራሽ" ድርጅት አያስፈልገውም። በተጨማሪም ኢህአፓ ዛሬም በትግል ላይ ያለ ድርጅት መሆኑን አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ሆኖ እያለ፣ ከሳሹ ድርጅትም የኢህአፓን መኖር እያወቀ፣ ለምን የኢህአፓን ስም ለመውሰድ እንደሚፈልግና "እውነተኛው ኢህአፓ እኔ ነኝ" ለማለት እንደሚሻ እስከአሁን አልገባንም። በመሆኑም በእኛ በኩል በፍትህ ደጅ ላይ ነንና አሁንም ኢህአፓ እየታገለ ያለ በመሆኑ፣ እስከመጨረሻው ለመከላከልም ሙግቴንና ክርክሬን ስቀጥል ለእናንተ ዳኞች ያለኝን ታላቅ አክብሮት በመግለጽ ነው በማለት፣ አጠንክሮ አቀርቧል። በእዚህ « እውነተኛው ኢህአፓ እኔ ነኝ፣ ስሙም ለኔ ይገባል » በሚለው የክርክር ሂደት ለረጅም ጊዜ ሲከራከሩ የቆዩት የከሳሽና ተከሳሽ ጉዳይ፣ "ወራሽ አያስፈልገኝም" ባለው ኢህአፓ አሸናፊነት ተጠናቀቀ፣ ፋይሉ መዘጋቱን ታዝበናል። ይህ አወዛጋቢ የነበረ ፋይል ከተዘጋ በኋላ፣ በትግል ላይ ያለው ኢህአፓ አሁንም ኢህአፓ ሆኖ ሲቀጥል፤ ቀድሞውንም ድርጅታዊ ነፃነት የለውም እየተባለ ሲታማ የነበረው ኢህዴን ነኝ ባዩ ደግሞ ዛሬ የት ላይ እንዳለ እኛ ታዛቢዎች ፍርዱንና ሚዛኑን ለእናንተ በመተው ወደሚቀጥለው የክስ ፋይል እንወስዳችሁ።

<u>ሁለተኛው የክስ መዝገብ/ፋይል፥</u>

| | |
|---|---|
| የከሳሽ ስም | ብአዴን(የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) |
| የተከሳሽ ስም | መአህድ(የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት) |
| ዳኛ | የኢትዮጵያ ህዝብ |
| የችሎት አደባባይ | አንጋፋዋ ኢትዮጵያ |
| ፋይሉ የተከፈተበት | 1983 ዓም (እኢአ) |

<u>አጭር ማስታወሻ፣ ለአንባቢዎቻችን</u>

በቅድሚያ ወደ ክርክሩ ይዘናችሁ ከመግባታችን በፊት ብአዴን (የብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) ቀደም ሲል በመጀመሪያ ስሙ በኢህዴን፣ ከኢህአፓ ጋር ክስ ከፍቶ ከተረታ በኋላ፣ ከጠበቃው ኢህአዴግ ጋር (ካለፈው የሙግት ሂደት በመነሳት) መአህድን እንዴት አቸንፎ መውጣት እንደሚችል በጥልቀት ከመከረ በኋላ፣ ባላንጣውን መአህድ አሸንፎ ሊወጣበት የሚያስችለውን ምክር ይዞ ወደ ክርክሩ ሲገባ፣ ስሙን ቀይሮ (ኢትዮጵያ የሚለውን ሃረግ) በማውጣት የመረጠው ስም፣ <u>ብአዴን</u> መሆኑን ያዙልን ። በቀጥታ ወደ ሙግቱ እንሂድ

እኔ ከሳሽ ብአዴን የምገኘው በኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ ሲሆን፣ የምኖረውም በክልል ምኒልክ ቤተ መንግሥት ውስጥ ነው። ዛሬ እኔ የማላውቃችሁ እናንተ ግን የምታውቁኝ ዳኞች ፊት ቀርቤ የክሴን ፋይል ለእናንተ ዳኞች ሳሰማ፣ ዋና ባላንጣ የሆነኝ

ድርጅት መአህድ ፣ በውነቱ የት እንደነበረ የማላውቀውና ህዝብም የማያውቀው ሆኖ እያለ በከተምኩበት አዲስ አበባ፣ አገር በሚያውቀኝና ተወልጀ ባደኩበት ቤተ መንግሥት ውስጥ የማንም ትምክህተኛ መጥቶ ባላባት ነኝ እያለ፣ ባደገበት ትምክህት ያዙኝ ልቀቁኝ የሚለውን ሁሉ ለአንዴና ለመጨረሻ፣ መልክ ታስይዙልኝ ዘንድ ይቻላችኋል ብዬ ነው ከእናንተ ከዳኞች ፊት ለመቅረብ የተገድድኩት። እርግጥ ለአገሩ ባዳ ለእናንተም እንግዳ ብሆንም እኔ ብአዴን የአማራውን ሕዝብ ልጠብቀውና ላድነው የወረድኩ ሃዋርያ መሆኔን ግን የአማራው ህዝብ ይመሰክርልኛል። መአህድ ነኝ የሚለው ድርጅት፣ እስከዛሬ ድረስ ሳያውቀው የኖረውን የአማራ ህዝብና ትምክህት ብቻ ሲያስተምረው፣ የሌለ ታሪክን፣ የኢትዮጵያ ታሪክ የ3000 ሽህ ዓመት ታሪክ ነው እያለ ሲግተው የቆየውን የአማራ ብሄረሰብ፣ እንዴት ቢንቀው ነው ዛሬ ከመሬት ተነሥቶ መጥቶልሃለሁና ተቀበለኝ እያለ አካኪ ዘርፍ የሚለው? በማለት ጠይቆ በጠበቃው ኢህአዴግ አማካኝነት ክሱን ደርድሯል። ጠበቃው ኢህአዴግም የዋዛ አልነበረም።

ተካሳሹ መአህድ (የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት)ደግሞ እንዲሁ፣ ያለ ጠበቃ ሲከራከር ለክሱ መልስ ከመስጠቱ በፊት መአህድ የተመሰረተበትን ዓላማ በዝርዝር እንዲህ አቅርቦታል።

እኔ ተከሳሽ መአህድ(የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት) ድርጅቱን የመሰረትኩበት ዓላማ፣ እንደ ከሳሼ ብአዴን ጠባብነትን ለማንገሥና በጠባብነት ፈረስ ተጭኘ ዛሬ ብአዴን ባደገበትና በተኮተኮተበት፣ በጎሳና በጎጥ፣ ዘር ቆጥሮ የድንጋይ ዘመን በሚባልበት ኋላቀር አስተሳሰብ ተሞልቼ አይደለም። መአህድ የተመሰረተበት ዓላማ ግልፅ ያልሆነለት ለከሳሼ ብአዴንና እንደ ብአዴን በድንጋይ ዘመን አስተሳሰብ ለሚያስቡ ከፍሎች እንጅ፣ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወለል ብሎ የሚታይ ነው። እኔ ተከሳሽ መአህድ ከሳሼ ብአዴን ትምክህተኛ እንዳይለኝ እንጅ፣ ምንን ምን ካላሉት ገብቶ ይፈተፍታል ዓይነት ነገር እየሆነ፣ ብዙ ነገር ችላ በማለታችን ነገሮችን ሁሉ ያለ መልካቸው መልክ፣ ያለ ስማቸው ስም እየለጠፈ አገር ሊያጠፉ መመምጣታቸውን ያወቅነው ገና ''በሽግግር መንግሥት ስም'' የመንግሥትነት ሥልጣን እንኳ ሳይኖራቸው በማን አለብኝነት ባህረ ነጋሽን ከአባቱና አቅፎ ካመጣው ወያኔ/ኢህአዴግ ጋር ሲያስገንጥል ነው። ገና ከጥዋቱ ነው አዲስ አበባ በገባችሁ ማግስት የጥፋት መልክተኛ መሆናችሁን የተረዳነው። ደግሞ ዛሬ አፍ አለን ብላችሁ ትናገራላችሁን? ጅራፍ ራሷ ገርፋ ረሷ ትጮሃለች አሉ። ምን ዓይነት ይሉኝታ ማጣትና አለማፈር ነው። ይቅርታ የተከበራችሁ ዳኞቼ። ለመሆኑ የኢትዮጵያው አርበኛ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመሪያው የቀዶ ጥገና ሃኪምና የጥቁር አንበሳ ባለውለታ ፕሮፌሰር አሥራት ነብሳቸውን ይማርልንና፣ መአህድን ከማቋቋማቸውና ከመምስረታቸው በፊት፣ ያኔ በጎጥና በጎሳ የተደራጃችሁ ድርጅቶች ወያኔ፣ ኢህዴን፣ ኦህዴድ፣ ማነው ደግሞ አንደኛው እባካችሁ! አዎ ያ የወታደሮች ስብስብ (በኋላ እንኳን ከነአካቴው ድምፁ የጠፋው)፣ ባንድ ላይ ሆናችሁ በግብራችሁና በመልካችሁ እንድ ሁናችሁ እያለ የተለያየን ነን ለማለትና ንቁውንና ኩሩውን የኢትዮጳያ ህዝብ ያታለላችሁ መስሏችሁ ኢህአዴግ የሚል ድሪቶ ለብሳችሁ መምጣታችሁን የዘነጋነው መሰላችሁ? ያኔ አይደለም እንዴ ኩሩውና አርበኛው ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ በዩነበርስቲው ተውክለው መጥተው (ያኔ መአህድ የሚባል

ድርጅት አልተመሰረተም) ባህረ ነጋሽን ለማስገንጠል በተቀመጣቸሁበት ሸንጎ « ይህ ሸንጎ ሆነ አካል በኢትዮጵያ መሰረታዊና ሉዓላዊ ጉዳዮች ላይ ምንም ዓይነት ውሳኔና እርምጃ መውሰድ የማይችልና ይህን ለማድረግ ህጋዊ ኃላፊነት ያልተሰጠው መሆኑን አጋልጠው፣ ስብሰባውን ረግጠው የወጡ? ከዚያ ሁሉ ሸንጎኛ መሃል የኤርትራን ማስገንጠል ደባ አልቀበልም በማለት ኢትዮጵያዊነታቸውን ያስመሰከሩ ታላቅና ብቸኛ ሰው አይደሉም? እንዴት እንዴት ነው ነገሩ ጃል! የዛሬው የኔ ከሳሽ ብአዴን የትናንትናው ኢህዴን በኢህአዴግ ስም ተንጠልጥሎ መጥቶ፣ በምኒልክ ቤተ መንግሥት መሸጎ ባህረ ነጋሽን ያስገነጠለ አይደለም? ምንስ ዓይነት የሞራል ብቃት ኖሮት ነው ዛሬ ደግሞ በተከበረው የችሎት አደባባይና በተከበሩት ዳኞች ፊት ቆሞ፣ አፍ አለኝ ብሎ እኔን ሙግት የሚገጥመኝ? አገር ሲያረጅ ጃርት ያብቅላል ይባላል።

ክቡር ዳኞች ሆይ! መአህድ የተቋቋመው በእውነቱ ብአዴን እንደሚለውና እንደ ብአዴን የአማራውን ህዝብ በጠባብነት ለመቅረፅና አማራ ነኝ ብሎ በአማራነቱ እንዲያስብ በዘር፣ በጎሳና በጎጥ እንዲኮለኮል አልነበርም። እንዲያውም የኢህዴኑ አባት የሆነው ወያኔ/ኢህአዴግ ነው ይህንን የጠባብነት ዛር ጭኖ ''የሽግግር መንግስት ባለው ሸንጎው'' የሚሳተፍ ሁሉ መጀመሪያውንም ኢትዮጵያ የሚል ስም ያለበት ድርጅትን የማያቅፍ አድርጎ ነው የቀረፀው። ኢትዮጵያ የሚል ከሆነም ወያኔ/ኢህአዴግ የሚቆጣጠረው ሊሆን እንደሚገባ ደንግጓል። ለዚህ ደግሞ ምስክሮቼ በዚሁ ኤርትራን ለማስገንጠል በተቀመጠው ሸንጎ ተብዬ ውስጥ የተሳተፉት ድርጅቶች ሁሉ የሚናገሩ ናቸውና ሌላ ምስክር አይሻኝም። ከሳሼ ኢህዴንም ልቡ ያውቀዋል። ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግሥና በምኒልክ ቤተ-መንግሥት ሊስፍር በሮጠበት ጊዜም ቢሆን፣ መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ ነውና (ቀድሞም መልካም ስም አልነበረውም)፣ ለንደን ላይ በአሜሪካ አደራዳሪነትና በእንግሊዝ ሽምጋይነት ሸንጎ ሲቀመጡ፣ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ድርጅቶችን አልቀብልም ብሎ አሻፈረኝ ማለቱን አገር የሚያውቀው ፀሐይ የሞቀው ነው። ኋላም ከእርሱ መሰል ድርጅቶችና ሻዕቢያ ጋር አብሮ ለመቀመጥ ፈቃደኛ ሆኖ በራሱ ላይ (ኢ)ን ጨመረና ኢህአዴግ ነኝ ብሎ የኢትዮጵያ ወኪል ሆኖ ለመቅረብ ተወተረተረ። ይልቁንም ኢህአዴግ የሚለውን ስም ላሰበው ተግባሩ ማስፈጸሚያ አድርጎት ይህውና ኢትዮጵያን የሚያጠፋበት መሳሪያ አደረገው። በኋላም ቢሆን አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ እንደሚባለው ዓይነት ራሱ ከልክሎ ራሱ መልሶ ደግሞ ፀረ ሰላም ምንትስ እያለ ያስጉኛል የሚላቸውን ሁሉ በሆነ ባልሆነ ክስ እየመሰረተ ማሰር፣ ሌባ ነው እያለ ማስገደልና መግደል፣ ማሳደድ የእለት እለት ስራው አደረገው። ይህ ያነሰ ይመስል ደግሞ ራሱ በከፈተውና በቀደደው የጎሳና የጎጥ ድርጅት ሁሉም እንዲኮለኮል ሲያደርግ እኛም ሳንፈልግ መአህድን ለማቋቋም ብንገደድም አሁንም ቢሆን እኛኑ ለማጥፋት ድንጋይ ሲፈንቅል ነው የኖረው። ዛሬ እናንተ ዳኞቼ እንደአያችሁትና እንደሰማችሁት የእውቁ ፕሮፌሰር አሥራት ህይወት መጥፊያ ሰበብ የሆነውም ይኸው መከረኛ ድርጅት መአህድ ነው። ብዙ አባሎቻችንም ተገድለዋል፣ ታስረውብናል። እረ ስንት ጉድ አለ ቀንና ጊዜ የሚያወጣው። ይህን ሁሉ በደል እያደረሰብን ያለው ይኸው ከሳሻችን ብአዴን ነኝ የሚለውና ለራሱ እንኳን ነፍስና ሥጋ የሌለው የወያኔ/ኢህአዴጉ አሽከር አይደል? ይህን እውነት ነው ለምን ተናገራችሁ፣ ለምን አወቃችሁብን ተብለን ''ትምክህተኛ'' የምንባለው። ይህን አሌ ማለት ይችላል? ባይነኩን ደግ ነበር ከነኩን ግን ሙግቱንማ! በሚቀጥለው....